
# ጠልአበ ፈለጶስ



በግዕዝና በአማርኛ

፲፱፻፺፱ ዓ.ም.



ቅዱስ ፊልጶስ
ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ
ሲያጠምቀው

መልክዐ ፊልጶስ ወንጌላዊ ዘአጥመቀ ስመኮንን ኢትዮጵያዊ ዘውስቱ ሕጽዋ ስሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ።

ፊልጶስ ወንጌላዊ አመ ስሕጽው አጠየቆ፣ በእንተ በግዕ የዋህ ስቃስ ኢሳይያስ ጽድቆ።
ይቤ ሕጽው ኀበ ነቅዐ ማይ አልጸቆ፣ ነዋ ማይ ወመኑ ይከልእኒ ተጠምቆ፣ አስመ መንፈስ ቅዱስ ኮነ ዘይፈጽም ጻሕቆ።

ሰላም ስዝክረ ስምክ ዘትርጓሜሁ በዮናኒ፣ ነያሌ አፍራስ ውእቱ ወአኮ በዕብራኒ።
ፊልጶስ ሳእክ አሠረ ክርስቶስ ዴጋኒ መሀረኒ ስውስድከ በቃስ አምላክ



የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ኢትዮጵያዊውን መኮንን ያጠመቀዉ የወንጌላዊዉ ፊልጶስ መልክዕ።

ወንጌላዊው ፊልጶስ ስለ የዋሁ በግ የኢሳይያስን ቃል አውነታ፣ ስጃንደረባው ባስረዳው ወደ ውሃ ምንጭ ደርሶ እንዲህ አለ።
አነሆ ውሃ መጠመቅን ማን ይከለክለኛል? መንፈስ ቅዱስ ዐሳቡን የሚፈጽምለት ሆኖአልና።

ትርጓሜው በአብራይስጥ ሳይሆን በግሪክኛ ፈረስ ገሪ ስሆነ ስምህ ሰላምታ ይገባል።
የክርስቶስን ፈለግ የምትከተል አገልጋይ ፊልጶስ ሆይ፣
ቀድሞ አማኒዉ ጃንደረባውን እንዳስተማርኸዉ እኛን ልጆችህን

አዶኒ ከመቀዲመ መሀርኮ ለሕጽው
አማኒ።።

ሰላም ለርእስከ ወለቅብዐ
ክቡር ሥዕርቱ።።
ዘላዕሌሁ ረበባ አእዳው ክልኤቱ
(ለድስቱ)።።

ፊልጶስ አሐዱ እምነ ሳእከን
ስብዐቱ አስተፋጥን ተልእኮተከ
ውስተ መቅደስከ ዘንቱ።።
አግዚአብሔር ዘሠምሮ ለገዲር
ውስቴቱ።።

ሰላም ለገጽከ ከመ ገጸ
መልአክ ዘተሰብሐ። ጸጋ መንፈስ
ቅዱስ በጽዮን አስመ ኪያሁ
አብርሃ። ለውዳሴከ ፊልጶስ አመ
ልቡናየ ተግሀ።።
ረስዮ ለልሳንየ ከመ ሰይፍ በሊሀ
ወለልቡናየ ረስዮ ስፋሐ።።
ሰላም ለቀራንብቲከ ወለአዕይንቲከ



በጌታ በፈጣሪ ቃል አስተምህ
ረን። ለሰራስህና ክብርን ለተቀባው
የወሥራ ሁለቱም ሐዋርያት እጆች
ላረፋበት ጠጉሩ ሰላምታ ይገባል።።
ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ፊልጶስ
ሆይ አግዚአብሔር በወሰጡ
ለማደር በወደደው በዚህ
በመቅደስህ ውስጥ አገልግሎትህን
አፍጥን።።

እንደ መልአክ ፊት
ላበራው ፊትህ ሰላምታ ይገባል።።
የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በጽዮን
እርሱን አብርቶታልና።።

ፊልጶስ ሆይ ልቡናዬን
ለምስጋና በተጋ ጊዜ አንደበቴን
እንደ ሰይፍ የተሳለ አድርገው።።
ልቡናዬንም ሰፊ አድርገው።።
ለቅንድቦችህና የከበረውን የጠጉን
ደም ምስጢር ሳዩ ለንስር

ዘንስር። እስ ነጸራ ምስጢሩ ዘደመ በግዕ ክቡር። ቅዱስ ፊልጶስ በጸሎትከ ሥሙር አስተምሕር ጎበ አምላክ አመ ወርኀ ሐዲስ ማእረር ደባርክ በ ጒራቱ ፍሬሃ ለምድር።

ሰላም ለአእዛኒክ እስ ሰምዓ በከዋላ ቃለ መንፈስ ቅዱስ ዘይቤ ትልዎ ለሠረገላ። ሰባኬ ወንጌል ፊልጶስ ለምድረ እስያ በማእከላ። ለብከትከ ሶበ ተሰምዐ በሀገ ረ ሳምር ኵላ ትዜምር ቂሳርያ ወትዬብብ ገሊላ።

ሰ ላ ም ለ መ ላ ት ሐ ኪ ወለአእናፈክ እስ ተምዕዛ። በመዓዛ ጽጌ ክርስቶስ ለገነት ሥነ ሐውዛ።



ዓይኖችህ ሰላምታ ይገባል።

ቅዱስ ፊልጶስ ሆይ በተወደደው ጸሎትህ በሰዲሱ መክር ወራት ጊዜ፡

የምድርን ፍሬ ይባርክ ዘንድ ወደ አምላክ ለምን።

ይህን ሰረገላ ተከተለው የሚለውን የመንፈስ ቅዱስን ቃል በስተጒላ ለሰሙ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል።

በእስያ ምድር መካከል ወንጌልን የሰበክህ ፊልጶስ ሆይ ለብከትህ በለማርያ ሀገር ሁሳ በተ ሰማ ጊዜ ቂሳርያ ትዘምራለች ገሊላም እልል ትላለች።

ለጒንጮችህና የገነት ውበት የሆነውን የአበባ ክርስቶስ መዓዛን ላሸተቱ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ ፍቁር ወልድ ዘምድ
ረ ሎዛ ትትሜሰል ከመ ወይጠል
ወከመ ዘሀየል ወሬዛ
እንዘ ሰማርያ ተዐርግ ወትወርድ
ጋዛ።

ሰላም ለከናፍረከ ወለአፉከ
ዘተከሥተ ከመ ለሕጽው ይስብክ
ዘኢሳይያስ ትንቢተ።

ፊልጶስ ለሰላማ አስተዳሎከ
ፍናተ ድኀረ ተወፈይነ በእደዊከ
ጥምቀተ አስመ በሰላማ ነሣእነ
ዘቁርባን ሥርዐተ።

ሰላም ለአስናኒከ ወለልሳንከ
ዘነበቡ። በእንተ በግዑ ለአብ ዘዲበ
መስቀል ተፀልቡ።

ፊልጶስ ለሕጽው ድኀ
ረ መሀርኮ ጥበበ ሕጽወ ለእሊሳዑ
ነገረ ጥበብ ወሀበ ወንበ ጥበብ
ጸውዐ ወአቅረበ ሕዝቡ።



ተወዳጅ የሎዛ ምድር ልጅ ፊልጶስ
ሆይ ወደ ሰማርያ ስትወጣና ወደ
ጋዛ ስትወርድ በፈቆና በዋልያ
አንበሳ ትመሰላለህ።

ለከንፈሮችህና የኢሳይያስን
ትንቢት ለጃንደረባው ይሰብክ
ዘንድ ለተንቀሳቀሰው አፍህ
ሰላምታ ይገባል። ፊልጶስ ሆይ
ለሰላማ መንገድን አዘጋጀህ
በእጆችህ ጥምቀትን ከተቀበልን
በኋላ በሰላማ የቁርባን
ሥርዐትን ተቀብለናልና።

ለጥርሶችህና በመስቀል ላይ
ስለ ተሰቀለው የአብ በግ ለተናገ
ረው አንደበትህ ሰላምታ ይገባል።
ፊልጶስ ሆይ ለጃንደረባው ጥበብን
ካስተማርኸው በኋላ ጃንደረባው
ለወገኖቹ የጥበብን ነገር ሰጠ።
ሕዝቡንም ወደ ጥበብ ጠርቶ

ሰላም በቃልከ ወሰእስትንፋስከ ምስለ ጕርሜነ ለክሣድከ ዓዲ ወለመታክፍቲከ ክልኤ። ፊልጶስ አሐዱ እም እለ ተጸውዑ በጽዋዔ ጸሊ ለውሉድከ በዕለተ ዐባይ ጉባኤ ምስለ ብፁዓን ንርከብ ዘለክብር ትንሣኤ።

ሰላም ለዘባንከ ዘዓምደ ኦሪት ፀወኑ ለእንግድዓከ ዓዲ ዘልብሰ ወንጌል ክዳኑ መጥምቀ ሕጽው ፊልጶስ ለእግዚአብሔር ካህኑ።

ለቃል ተሠግዎቶ እምድንግል ትዜኑ፣ ወትነግር ትሕትናሁ ውስተ ጎል መካኑ።

ሰላም ለሕፅንከ ዘበጥቃሁ ረፈቀ፣ ሕጽመ ሕንደኪ ብሥራተ አመ ክመ ደስማዕ ጽሕቀ።

ፊልጶስ ወንጌላዊ አስመ አንዘ ዲያቆን አጥመቀ፣



አቀረበ።

ለቃልህና ከጕርሮ ጋር ለትንፋሽህ ሰላምታ ይገባል። ዳግመኛም ለአባትህና ለሁለቱ ትከሻ ዎችህ ሰላምታ ይገባል።

በጥሩ ከተጠሩት አንዱ ፊልጶስ ሆይ በታላቁ ጉባኤ ቀን ከብፁዓን ጋር የክብር ትንሣኤን እንድንነሣ ለልጆችህ ፀልይ። የኦሪት ምሰሶ መጠጊያው ለሆነ ጀርባህ የወንጌል ልብስ ሽፋኑ ለሆነ ደረትህም ይገባል።

ጃንደረባውን ያጠመቅኸው የእግዚአብሔር ካህን ፊልጶስ ሆይ፣ ከድንግል የቃልን ሰው መሆን ታወራለህ። በቦታው በግርግም ውስጥም ትህትናውን ትናገራለህ፣ የሕንደኬ ጃንደረባ ወንጌልን ይሰማ ዘንድ በተጋ ጊዜ፣

እምሐዋርያት ኢናሐፅፅክ ሕቀ፣ እስመ ከመ እሱ አምላክ ኪያክ አልዘቀ።

ሰላም ለአዳዊክ ተአምረ እስ ገብረ፣ እስክ ዕውራን ርእዩ፣ ወእስክ ሐንካሳን ሖሩ።

ተአምረክ ፊልጶስ ሰብአ ሰማርያ አንክረ፣ እስመ ብዙኃን ሰብአ ሥራይ ሶበ ኀደስክ ነጸረ፣ ለሐዋርያት ምስሌሙ ኀብረ።

ሰላም ለመዛርዒክ እስ ጸንው ስተልእኮ፣ ምስለ እስጢፋኖስ እጕክ በዘሐዋርያት ባርኮ።

ተወካፌ ነግድ ፊልጶስ ለጳውሎስ ዘአንደርኮ፣ ለወልድክ ተወከፈኒ ከመ ኢይርአይ ተሀውኮ፣ ውስተ ሰማያዊት ቤትክ ምድራዊት ዘአኮ።



ባጠገቡ ሰላምታ ለተቀመጠበት ዕቅፍህ ይገባል።

ወንጌላዊ ፊልጶስ ሆይ ዲያቆን ስትሆን ሰጥምቀሃልና፣ አምላክ አንደ እነዚህ ስላከበረህ ከሐዋርያት ጥቂት አናሳንስህም።

ዕውራን እስኪያዩ አንካሶችም እስኪራመዱ ድረስ፣ ተአምራትን ለሰደረጉ እጆችህ ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ ሆይ የሰማርያ ሰዎች ተአምራትህን አደነቁ፣ ብዙዎች የመተት ሰዎች ኀይልህን ባዩ ጊዜ፣ ከሐዋርያት ጋር አንድ ሆነዋልና።

ከወንድምህ እስጢፋኖስ ጋር ሐዋርያት ቡራኬ፣ ለሰገልግሎት ስበ ረቱ ጡንዎቻዎችህ ሰላምታ ይገባል።

ጳውሎስን ያሳደርኸው አንግዳ ተቀባይ ፊልጶስ ሆይ፣ መታ ወክን አንዳሳይ፣ ምድራዊት ባይደለች በሰማያዊት ቤትህ እኔን ልጅህን ተቀበለኝ።

ሰላም ለኵርናዕከ ወለአመትከ ምስለ አራን፣ ዘተሐፍን ማየ ለአጥምቆ ሕጽው የዋህ።

ፊልጶስ ሳእከ ዘአዕበየከ መሲሕ፣ ዕቀበነ ለውሉድከ አም አፈ አርዌ ቀይህ፣ ከመ መርዔቶ የዐቅብ ናሳዊ ትጉህ።

ሰላም ለአፃብዒከ ዘትእምርተ መስቀል ያስተዋድዱ፣ ምስለ አፅፋ ረሆን በዕሥር አለ ይትፈቀዱ። ፊልጶስ ሱቃስ አም ወንጌላውያን አሐዱ፣ ዘክረከ በውስተ ግብር እንተ ጸሐፈ በአዱ፣ ዘክሮ ቅዱሳን ለሱቃስ አኮኑ ልማዱ።

ሰላም ለገቦከ ወለከርሥከ መዝገብ፣ ዘያገምር ኩሉ ምሥጢረ ትዕግሥት ፕበብ። ፊልጶስ የዋህ ዘታቦተ ናህ ርግብ፣ ዜናከ ሕፀተ አደነ ጎሲና እኩደ ልብ፣



ለክርንህና የዋሁን ጃንደረባ ለማጥመቅ፣ ውኃን ለታፈነው ክንድህ ሰላምታ ይገባል።

ክርስቶስ ያከበረህ ፊልጶስ አገልጋይ ሆይ፣ ትጉህ እረኛ መንግሥቱን እንደሚጠብቅ፣ አኛን ልጆችህን ከቀዩ አውሬ አፍ ጠብቀን።

በዐሥር ከሚቁጠሩ ፕፍርቃቸው ጋር የመስቀል ምልክት ለሚያስማሙ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ ሆይ ከወንጌላውያን አንዱ ሱቃስ፣ በአጹ በጻፈው በግብረ ሐዋርያት አሰብህ። ቅዱሳንን ማሰብ ለሱቃስ ልማዱ ነውና።

ለንጉህና የፕበብ ትዕግሥት ምሥጢርን ሁሉ፣ ለሚወስነው መዝገብ ሆድህ ሰላምታ ይገባል።

እንዘ ጽጌ ረዳ መስቀል ትጸውር ለሕዝብ።

ሰላም ለልብከ ወለኵልያቲከ አዕጹቅ፣ ለአማዑቲከ ርኅሩኅ ወለሕንብርትከ ፍሑቅ። ፊልጶስ ወንጌላዊ መልአክ ሥርዐት መጥምቅ፣ ጸውዐከ መንፈሰ ጽድቅ ለተልእኮ ምሥጢር ረቂቅ። እምድኅረ ዕርገቱ ለወልድ ኀበ አብ ጻድቅ።

ሰላም ለሐቂከ ለግብረ ተ ልእኮ ቅኑተ ለንጽ፣ ወዓዲ ሰላም ለዘዚኣከ አቄያጽ።

ፊልጶስ ኀረይ ምስለ ስድስቱ አብያጽ፣ ኀረያን ኀበ ሀለወ ማኅደ ረ ብርሃን ሕኑጽ፣ ከመ ንኅድር ጸውዐነ በሐዋዝ ድምፅ።

ሰላም ለአብራኪከ ወለአጋሪከ ከዋው፣



የዋሁ የኖህ መርከብ ርግብ ፊልጶስ ሆይ ጽጌረዳ መስቀልን ተሸክመህ፣ የክፉ ልብ ዐሳብ የጥፋት ውኃ መጉደልን ለሕዝብ አበሠርህ።

ለልብህና ቅርንጫፎች ኩላሊቶችህ፣ ለርኅሩኅን አንጀትህና ለተቀረጸው ሕንብርትህ፣ ሰላምታ ይገባል።

ወንጌላዊውና አጥማቂው የሥርዐት አገልጋይ ፊልጶስ ሆይ፣ ለአገልግሎት ሥራ ሸርጥ ለታጠቀው ወገብህ ሰላምታ ይገባል።

ዳግመኛም ለጥናችህ ሰላምታ ይገባል። ከስድስቱ ወንድሞች ጋር የተመረጥኸው ፊልጶስ ሆይ፣ የተመረጡት ባሉበት በታነጸው የብርሃን ማደርያ አናድር ዘንድ፣ በመልካም ድምፅ ጥሪን።

ስጉልበቶችህ ሰላምታ ይገባል።

እንዘ ኀበ ጋዛ ትወርድ እምዘ ፊልጶስ ፍናዊ ነገረ አምላክ ሕያው፤ አአምን በኢየሱስ ወልደ አብ ሥግው፤ እንዘ ይብል በእዴከ ተጠምቀ ሕጽው።

ሰላም ለ ሰ ከ ◦ ና ከ ወለመከድየከ ዕጉሥ፤ሠከ አሚከላ በሲህ በፍናተ ሳምር መብአስ።

ለኢትዮጵያ ፊልጶስ ተራዳኢሃ ቅዱስ። አስተምሕር በእንተ ሕዝባ ምሕረተ ሥጋ ወነፍስ፤ ኀበ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

ሰላም ለአፃብሚከ ወለአፅፋረ አግርከ ዘኢተዐቅፋ፤ በዕብነ ዐመሳ ዘአምን ወገባያን ወግረ ዘሰፋ።

ፊልጶስ አብ አዋልዲከ ተጽሕፋ፤ ምስለ ብፁዓት ደናግለ ፍቅር ወተስፋ፤



ክሰማርያ መንገዶች ወደ ጋዛ ስትወርድ ቀልጣፋ ስሆኑ አግሮችህም ሰላምታ ይገባል።

የሕያው አምላክን ነገር የምትናገር ፊልጶስ ሆይ፤ ሰወ በሆነ በአብ ልጅ በኢየሱስ አምናለሁ ብሎ፤ ጃንደረባው በእጅህ ተጠመቀ።

ለሰኩናህና ጕዳጕፅ በሆነው በሰማርያ መንገድ ሹል የሆነውን አሾህ ለታገሠው ጫማህ፤ ሰላምታ ይገባል።

የኢትዮጵያ ተራዳኢ ቅዱስ ፊልጶስ ሆይ፤ ስለ ሕዝቧ የሥጋና የነፍስ ምሕረትን፤ ከአብና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስም ዘንድ ስምን።

ለጣቶችህና ለአምንና በዘሰፋ ኩረብታ በገባን የዐመፅ ድንጋይ ሳልተሰናከሱ የአግርህ ፐፍሮች ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ አባት ሆይ ሴቶች ልጆችህ የጴጥሮስ እመቤት

ለአብ ፅ፱ ድንግል ማርያም እግዝእቱ ለኪፋ።

ሰላም ለቅምከ ወለመልክዕከ አዳም፣ አምሳለ መልክዑ ለሙሴ ትሩፈ ጽሶት ወጾም።

ፊልጶስ ዘውገ ሙሴ ወአረጋዊ ፍጹም፣ ነዓ ፣ነዓ ምስለ ገብረ ክርስቶስ ዘርም፣ለመቅደስከ ትባርክ ዮም።

ሰላም ለፀአተ ነፍስከ በተ ወክፎ ሥቃይ ዘለምዕ፣ ከመ እስጢፋኖስ ሰማዕት በእንተ ክርስቶስ እግዚእ።

ፊልጶስ ጸሊ ምስለ አዋልድ አርባዕ፣ ደመናት ኢይትክልኡ አንጠብጥቦ ዘናም ለዘርዕ፣ ከመ ይትፈሥሑ እንስሳ ወሰብእ።



ከብፅዓት የፍቅርና የተስፋ ደናግል ጋር ተቁጠረ።

ለቁመትህ ሰላምታ ይገባል፣ ጸሎትና ጾምን ያበዛው የሙሴን መልክ ለሚመስለው ላማረው መልክህም ሰላምታ ይገባል። የሙሴና የፍጹሙ አረጋዊ ወገን ፊልጶስ ሆይ፣ ዛሬ መቅደስህን ትባርኝት ዘንድ፣ ከሾሙ ገብረ ክርስቶስ ጋር ና፣ና።

እንደ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ስለ ጌታ ክርስቶስ፣ የሰማዕትነት ሥቃይን በመቀበል ስነፍስህ መወጣት ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ ሆይ እንሰሳዎችና ሰዎች ደስ ይሰኙ ዘንድ፣ ደመናት ለዘርዕ ዝናምን ማንጠባጠብ እንዳይከለከሉ፣ ከአራቱ ሴቶች ልጆች ጋር ጸልይ።

ሰላም ለበድነ ሥጋክ ወለዘሥጋክ ግንዘት፣ በአፈወ ዕፍረት ምውዝ በዘዕብራውያን ሥርዐት።

ፊልጶስ ጸሊ ምስለ አስጢፋኖስ ሰማዕት፣ ይረድ በሳዕሌነ መንፈሰ ሐዲስ ትንቢት፣ ከመ ለአዋልድ አርባዕ ወረደ ትንት።

ለመቃብረክ በሀገረ ዐባይ ቂሣርያ፣ ውስተ አሐቲ መካን እግዚአብሔር ዘጎረያ።

ሰባኬ ወንጌል ሐዲስ ፊልጶስ ሐዋርያ፣ ደገንዩ ኢትዮጵያ ለወልደ ድንግል ማርያም፣ ሰሚዖሙ ትምህርተክ አምሕጽሠ ኬንያ።



ለሥጋህ በድንና በዕብራውያን ሥርዐት ባማረ ሽቱ ለሥጋህ መገነዝ ሰላምታ ይገባል።

ፊልጶስ ሆይ የሐዲስ ትንቢት መንፈስ ቀድሞ ለአራቱ ሴቶች እንደ ወረደ፣ በእኛ ላይ ይወርድ ዘንድ ከሰማዕቱ አስጢፋኖስ ጋር ጸልይ።

በታላቂቱ ቂሣርያ ሀገር እግዚአብሔር በረጣት በንዲት ቦታ ውስጥ ለመቃብርህ ሰላምታ ይገባል።

የሐዲስ ወንጌል ሰባኪ ፊልጶስ ሆይ ትምህርትህን ከብልሁ ጃንደረባ ሰምተው፣ ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም ልጅ ይገዛሉ።

ፊልጶስ አስጢፋኖስ፣ ጳርኮ
ሮን ወኒቃርና፣ ሕጽወ ሕንደኬ
ንግሥት ጳርሜና ወጢሞና።
ንዑ፣ ንዑ ምስሰ ማርያም
ሶልያና፣
ለኢትዮጵያ ፈጻሚተ ሕግ ዘሲና፣
ከመ ትዕቀብዋ እምኵሉ ሙስና።

ጽጎረ ብዙኃን ፈተዉ ወተ
መነዩ ተዝካረ ፊልጶስ ደግበሩ፣
ዜና ዕበዩ እምሉቃስ እንዘ ይዜ
ክሩ።
በሳድስ ወርኀ ለበዓለ ድንግል ጊዜ
ድራሩ፣
ተፈጸመ ዘተመነዩ፣ እስመ በሳሲም
ሀገሩ፣
በኢትዮጵያ ተሐንጸት ለፊልጶስ
ደብሩ።



ፊልጶስና አስጢፋኖስ አርኮ
ሮንና ኒቃርና፣ የንግሥት ሕንደኬ
ጃንደረባ ጳርሜንና፣ የሲናን ሕግ
ፈጻሚት የሆነችውን ኢትዮጵያን
ክጥፋት ሁሉ ትጠብቂት ዘንድ፣
ከሶልያና ማርያም ጋር ኑ፣ ኑ።

ብዙዎች የክብሩን ዜና
ከሉቃስ እያስታወሱ፣ የፊልጶስን
መታሰቢያ ያደርጉ ዘንድ
በስድስተኛው ወር በድንግል በዓል
በዋዜማው፣ የተመኙት ተፈጸመ።

በሀገሩ በሲየሩሳሌምና
በኢትዮጵያ የፊልጶስ ደብር
ታንጻለችና።

# ደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊሊጶስ ቤተክርስቲያን አጭር መግለጫ

ደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊልጶስ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ብቸኛው በዲያቆናዊው /ወንጌላዊው/ ቅዱስ ፊልጶስ ስም የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን ነው።

ወንጌላዊ ቅዱስ ፊልጶስ በቂሳሪያ ከተማ የተወለደ ከቅዱስ እስጢፋኖስ ጋር ሊቀ ዲቁና ከተቀበሉት ከሰባቱ ሊቀ ዲያቆናት መካከል አንዱ ሲሆን በጋዛ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ በማስተ ማርና በማጥመቅ ክርስትናን ለኢትዮጵያውያን በመስበክ ቅድሚያውን የያዘ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ የሆነ ሐዋርያ ነው። ሐዋ 6÷5 ሐዋ. 8÷26-40

ይህን ታላቅ ውለታ በማስታወስና በመዘከር ዛሬም የበረከቱና የቃል ኪዳኑ ተሳታፊ እንሆን ዘንድ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ አነሳሽነትና መልካም ፈቃድ ይህ ቤተክርስቲያን በ1978ዓ.ም ተመስርቷል።

ቤተክርስቲያኑ በዚህ ስፍራ ከተተ ከለበት ጊዜ አንስቶ በሐዋርያው ጸሎትና ምልጃ ለምዕመናኑ መንፈሳዊ በረከትን እየሰጠና የሚጠበቅበትን አገልግሎት በማከናውን ላይ ይገኛል።

የደብሩ የሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ዓመታዊ ክብረ በዓል የሚከበረው ጥቅምት 14 እና የካቲት 20 ቀን በመሆኑ ምዕመናን ሁሉ ወደዚህ ታሪካዊ ደብር በመምጣት የበረከቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናስተላልፋለን።

*የሐዋርያው ረድኤትና በረከት አይለየን*

